በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# ተጠበቁ - ክፍል 3!!!

## ኦርቶዶክሳዊት ቤ/ክ ስለ ፕሮቴስታንቲዝም ምን ትላለች?


**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ጥር ፳፱ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.

# ኦርቶዶክሳዊት ቤ/ክ ስለ ፕሮቴስታንቲዝም ምን ትላለች?

## *መግቢያ*

- ፕሮቴስታንቲዝም የመጽሐፍ ቅዱስን እውነታ አዛብቶ ግላዊ አመለካከቶችን የሚያስተጋቡ ልዩ ልዩ ሥጋዊ አመለካከቶች በክርስትና እምነትና በመንፈሳዊነት ስም የሚራመዱበት መንገድ ነው፡፡ ከእነዚህም የሚከተሉት ተጠቃሾች ናቸው፡፡
    - የመጽሐፍ ቅዱስ ጥሬ ቃል ብቻ ማለት
    - እምነት ብቻ ማለት
    - ጸጋ ብቻ ማለት
    - ‹‹ክርስቶስ›› ብቻ ማለት
    - ክብር ለእግዚአብሔር ብቻ
    - ዘላለማዊት ርስት
    - በ40ና በ80 ቀን (ሕጻናትን) ማጥመቅ አይቻልም ማለት
    - ቅዱስ ቁርባን ለድኅነት አይሆንም ማለት ናቸው፡፡
- ስለዚህም በጥቂቱ የሚከተሉትን እውነተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች መገንዘብ ኦርቶዶክሳዊቱ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን የብርሃን ወንጌልን ለዓለም ለማድረስ የተቀበለችውን አደራና ኃላፊነት ያሰ ስህተት ለመወጣት ያስችለናል፡፡

# <u>ኦርቶዶክሳዊት ቤ/ክ ስለ ፕሮቴስታንቲዝም ምን ትላለች?</u>

## *የመጽሐፍ ቅዱስ ጥሬ ቃል ብቻ*

- ‹‹*<u>ሌዋውያኑም</u>* ሕጉን ያስተውሉ ዘንድ ሕዝቡን ያስተምሩ ነበር ሕዝቡም በየስፍራቸው ቆመው ነበር፡፡ የእግዚአብሔርንም ሕግ መጽሐፍ አነበቡ ዕዝራም እግዚአብሔርን ማወቅ ያስተምርና ያስታውቅ ነበር፥ ሕዝቡም የሚነበበውን ያስተውሉ ነበር፡፡›› *<u>ነህ 8፡7-8፡፡</u>* እንደተባለው መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ሌሎች መጻሕፍት መተርጎምና ምስጢሩም መነገር ያስፈልገዋል፡፡
- ፈሪሳውያን ስለ ሰንበት ስላነሱት ጥያቄም ጌታችን የትእዛዙን ትክክለኛ ትርጉም ‹‹ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም ያለው ምን እንደሆነ ብታውቁስ ኃጢአት የሌለባቸውን ባልኰነናችሁም ነበር፡፡የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነውና፡፡ከዚያም አልፎ ወደ ምኵራባቸው ገባ፡፡እነሆም፥ እጁ የሰለለች ሰው ነበረ፤ ይከሱትም ዘንድ፡፡ በሰንበት መፈወስ ተፈቅዶአልን? ብለው ጠየቁት፡፡እርሱ ግን፦ ከእናንተ አንድ በግ ያለው በሰንበት በጉድጓድ ቢወድቅበት፥ ይዞ የማያወጣው ሰው ማን ነው?እንግዲህ ሰው ከበግ ይልቅ እንደምን አይበልጥም! ስለዚህ በሰንበት መልካም መሥራት ተፈቅዶአል አላቸው፡፡›› *<u>ማቴ 12፡7-12፡፡</u>* በማለት አስረድቷል፡፡
- የክርስትናው ሥነ አምላክ ታሪክ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ታሪክ ሆኖ ሊጠቀስ የሚችልበት ዕድል አለ፡፡

# ኦርቶዶክሳዊት ቤ/ክ ስለ ፕሮቴስታንቲዝም ምን ትላለች?

## *የመጽሐፍ ቅዱስ ጥሬ ቃል ብቻ*

- አርያኖስ ‹‹ሐዋርያዊቱ ቤተ ክርስቲያን የእምነት ሥርዓትዋንና ትምህርትዋን ጠብቃ ያቆየችው ቀኖናውያት ከሆኑት ቅዱሳት መጻሕፍት ባገኘቻቸው ትርጓሜዎች ነው፡፡›› በማለት አጽንዖት ሰጥቶ ተናግሯል፡፡
- ቤተ ክርስቲያን ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የምትቀበለው ወንጌል ከክርስቶስ የተቀበለችው ያልተበረዘና ያልተለወጠ ወንጌል ነው፡፡
- አርያኖስም ይኸው በእውነተኛ ወንጌል ላይ የተመሠረተው ትምህርትና ስብከት በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና መምህራን ተጠብቆ እንዲቀጥል ተናግሯል፡፡
- ጠርጡሉስም ይህንኑ መንገድ በመከተል ‹‹መጽሐፍ ቅዱስን ትርጉሙን ሳናውቅ በማንበብ ብቻ መረዳት አይቻልም፤ ጥሬ ቃሉን በማንበብም አከራካሪ የሆኑ የሚመስሉ ጥቅሶችም ሊገጥሙን ይችላሉ፡፡ ተጠራጣሪዎችም ይህንኑ በግርፉ በመውሰድ መጽሐፉ እንዲህ ይላል እያሉ እንደፈለጉት ይጠቀሙበታል፡፡›› በማለት አደገኛነቱን አስታውሶናል፡፡
- ስለዚህም ‹‹የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ትክክለኛ ትርጉም የሚገኘው እውነተኛ ክርስትናና እንደዓለት በተመሠረተባት ቤትና እምነት ውስጥ ነው፡፡›› በማለት አስጠንቅቆናል፡፡

# ኦርቶዶክሳዊት ቤ/ክ ስለ ፕሮቴስታንቲዝም ምን ትላለች?

## *የመጽሐፍ ቅዱስ ጥሬ ቃል ብቻ*

- አርዮስን ተከራክሮ የረታው ቅዱስ አትናቴዎስም ‹‹አርዮስ በቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ላይ ለተመሠረተው ትምህርት ታማኝ ሆኖ ቢገኝ ኖሮ ስለክርስቶስ የሚሰማውን ስህተት ባልተፈጠረ ነበር፡፡›› በማለት እንደሌሎቹ አጽንዖት ሰጥቶ ተናግሯል፡፡
- ትውፊት ከሐዋርያት የተረከብነው ቤተ ክርስቲያንም ትክክለኛ ወደ ሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ወይም ትርጉም የተመራችበት ነበር፡፡
- ትውፊት ከመጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ ‹‹ድብቅ የመገለጥ ምስጢር ምንጭ›› ሆኖ የተቆጠረ ሳይሆን ይልቁኑ እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት የሌላቸው ግለሰባዊ ትርጓሜዎችን ከማስተጋባት ይልቅ ለሐዋርያት ትምህርት ታማኝ ሆና የቆየች መሆንዋን የሚያረጋግጥልን ምንጭ ነው፡፡
- ማርቲን ሉተር ‹‹ማንኛውም ሰው በትውፊት ላይ ሳይመሠረት እንደመሰለውና እንደገባው መጽሐፍ ቅዱስን መተርጎም ይችላል›› በማለት የሚሞግት ሲሆን ይህም አቅጣጫ ከቤተ ክርስቲያን ተጠያቂነትና ዳኝነት ይልቅ ግለሰባዊ የሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከቶችና አስተሳሰቦች ቁጥራቸው በርካታ በሆኑ የፕሮቴስታንት ክፍሎች እንዲስፋፉ አድርጓል፡፡

# <u>ኦርቶዶክሳዊት ቤ/ክ ስለ ፕሮቴስታንቲዝም ምን ትላለች?</u>

## *እምነትና ጸጋ ብቻ*

- *መዳን በእምነት ብቻ ይገኛል ብለው የሚያምኑ አስተሳሰባቸውን በአንድ ጥቅስ ወይም በአንዱ ጥቅስ የተወሰነ ገጽ ላይ የመሠረቱ ናቸው፡፡*
- ለምሳሌ ‹‹ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም፡፡›› *<u>ኤፌ 2፡8-9፡፡</u>* የሚለው ይህ ጥቅስ ብቻውን እምነት ብቻ የሚለውን አቅጣጫ የሚደግፍ ሊመስል ይችላል፤ ነገር ግን ቀጥሎ የሚገኘው ኃይለ ቃል ግን ‹‹ እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን ›› *<u>ኤፌ 2፡10፡፡</u>* በማለት የሥራንም አስፈላጊነት ይነግረናል፡፡
- እምነት የሚለው ቃል ባላብዙ ዘርፍ ትርጉም ያለው ቃል ነው፡፡ ለምሳሌ፡-
  1. ሕያው እምነት፡- ‹‹እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ ነው፡፡›› እንዳለ፡፡ *<u>ያዕ 2፡20፡፡</u>* እንዲህ ያለ ሥራ የማይገኝበት እምነት ማንንም ማዳን የማይችል ‹‹እምነት አለኝ የሚል፥ ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን?›› *<u>ያዕ 2፡14</u>* ተብሎ የተገለጸ ነው፡፡

# ኦርቶዶክሳዊት ቤ/ክ ስለ ፕሮቴስታንቲዝም ምን ትላለች?

## *እምነትና ጸጋ ብቻ*

- እምነት የሚለው ቃል ባላብዙ ዘርፍ ትርጉም ያለው ቃል ነው። ለምሳሌ፡-
    1. ሕያው እምነት፡- ቅዱስ ያዕቆብ በተጨማሪም ‹‹እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል።›› *ያዕ 2፡19።* ብሎ በመጻፍ ታዲያ ካመነ ሰይጣንም ድኗል ልንል ነውን ብሎ ይጠይቃል።
    2. በፍቅር የሚሠራ እምነት፡- ‹‹በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ፥ በፍቅር የሚሠራ እምነት እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና።›› *ገላ 5፡6።* የተባለው ሲሆን
    3. እምነትና ፍቅር፡- ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ።›› *ቀዳ ቆሮ 13፡2።* እንደጻፈው የተገለጸው እምነት ደግሞ ሌላው መግለጫ ነው።
- ጌታችንም ስለ ምጽአቱ ባስተማረበት ክፍል አስቀድሞን በምድር ሳለን እንደሠራነው መጠን እንደሚከፍለን ‹‹‹‹የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል፤አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል፥በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል።ንጉሡም በቀኙ ያሉትን … እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፥ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፥ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፥ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥ ታስሬ ወደ እኔ … እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል።እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።›› *ማቴ 25፡31-46።* ብሎናል።

# ኦርቶዶክሳዊት ቤ/ክ ስለ ፕሮቴስታንቲዝም ምን ትላለች?

## *እምነትና ጸጋ ብቻ*

- ቅዱስ ጴጥሮስም ስለ ፍርድ ቀንና ስለ *ሥራ* ‹‹ለሰው ፊትም ሳያደላ በእያንዳንዱ ላይ እንደ ሥራው የሚፈርደውን አባት ብላችሁ ብትጠሩ በእንግድነታችሁ ዘመን በፍርሃት ኑሩ።›› *ቀዳ ጴጥ 1፡17።* በማለት ጽፎልናል።
- ብዙዎች በጌታችን ቀኝ የተሰቀለውን ወንበዴ በእምነት ብቻ ለጸደቁት ምሳሌ አድርገው ይጠቅሱታል። ነገር ግን ይህ ወንበዴ *ያመነ* ብቻ ሳይሆን ‹‹ኢየሱስንም። ጌታ ሆይ፥ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ አለው።›› *ሉቃ 23፡42።* በማለት ኃጢአቱን የተናዘዘ ሰው ነው።
- ኃጢአቱንም ከመናዘዝ በተጨማሪ ቅጣቱ የሚገባው መሆኑንም ተቀብሷል። በሌላ በኩልም በግራ የተሰቀለውን ሌላውን ወንበዴ ‹‹ከተሰቀሉት ከክፉ አድራጊዎቹም አንዱ። አንተስ ክርስቶስ አይደለህምን? ራስህንም እኛንም አድን ብሎ ሰደበው።ሁለተኛው ግን መልሶ፦ አንተ እንደዚህ ባለ ፍርድ ሳለህ እግዚአብሔርን ከቶ አትፈራውምን?ስለ አደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለንና በእኛስ እውነተኛ ፍርድ ነው...›› ሉቃ 23፡39-41። ብሎ ገስጾታል።
- በተጨማሪም ስለ ጌታችን ‹‹ይህ ግን ምንም ክፉት አላደረገም።›› በማለት ምስክር በመሆን ወንጌላዊ ኃላፊነቱን በሥራ ተወጥቷል። *ሉቃ 23፡41።*

# ኦርቶዶክሳዊት ቤ/ክ ስለ ፕሮቴስታንቲዝም ምን ትላለች?

## *ክርስቶስ ብቻና ክብር ለእግዚአብሔር ብቻ*

- ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲተተን ዘርና ነገድ ሳይለይ ሰዎችን ለክህነት ያጫቸው ቢሆንም ጥቂቶቹን ብቻ ግን ለሐዋርያነት፣ ሌሎችንም ለመፈወስ፣ ሌሎችንም ለማስተማር ሥራ ለይቶ መምረጡን መጽሐፍ ቅዱሳችን ይነግረናል፡፡
- ይህንም በአማንያኑ መካከል አግባብ ባለው ሥርዓትና መሠረት ላይ ለማነጽ ጥቂቶች (ጳጳሳት፣ ቀሳውስትና ዲያቆናት) ብቻ እጅን በመጫን ለተወሰነ አገልግሎት ተሹመዋል፡፡
- ኃጢአትንም ይቅር የሚሉበትና የሚይዙበትንም ሥልጣን ለሁሉም አማንያን ሳይሆን ለሐዋርያቱ ብቻ ሰጠ፡፡ ሐዋርያቱም ይህን ሥልጣን ለዲያቆናት ሳይሆን ለጳጳሳት ሰጡ፡፡
- በየጊዜውም የምዕመናኑ ቁጥር በአንድ ጳጳስ መመራት ከሚችልበት መጠን በላይ ሲሆን ለቅዱስ ቁርባንና በዚህ መልክ ላለው አገልግሎት ሁሉ እጅን በመጫን በጳጳሳቱ ቦታ በየአጥቢያው አገልግሎት እንዲሰጡ ተሾሙ፡፡ *ማቴ 16፡19፡፡*
- በብሉይ እንደሆነው እንደሌዋውያኑና እንደመልከጸዴቅ ክህነት ሁሉ በአዲሲቱ እስራኤል በቤተ ክርስቲያንም ቀሳውስትና ተሹመው የሚሾሙ የጳጳሳት ክህነት አለን፡፡

# ኦርቶዶክሳዊት ቤ/ክ ስለ ፕሮቴስታንቲዝም ምን ትላለች?

## *ዘላለማዊት ርስት*

- ጌታችን ‹‹እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለምም አይጠፉም፥ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም።›› *ዮሐ 10፡28፡፡* እንዲሁም ‹‹የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፥ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም።›› *ዮሐ 10፡29* በማለት ተናግሯል፡፡
- ይሁን እንጂ *በዕብ 6፡4-6* ደግሞ ‹‹አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን ሰማያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትንመልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱትንበኋላም የካዱትን እንደገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው፤ ለራሳቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታልና ያዋርዱትማልና።›› በማለት ተጽፎልን እናነባለን፡፡
- ታዲያ ለዘላለም አይጠፉም የተባሉት እነማን ናቸው? ለዚህ ‹‹በጎቼ ድምጼን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል፤›› *ዮሐ 10፡27፡፡* የሚለው ኃይለ ቃል የማይጠፉበትን መመዘኛና ምላሹን ያስረዳናል፡፡
- **ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን (መድኃኔዓለም) የሚሰሙትና በመስማታቸውም የሚቀጥሉ የሚከተሉትም ፈጽመው አይጠፉም፡፡**

# <u>ኦርቶዶክሳዊት ቤ/ክ ስለ ፕሮቴስታንቲዝም ምን ትላለች?</u>

## *ዘላለማዊ ርስት*

- ቅዱስ ጳውሎስ <u>*በዕብ 3:12 እና 6:6*</u> ሆን ብሎ እምነትን (ሃይማኖትን) ስለመተው ሲጽፍ አንድ ኃጥእ የአዲስ ኪዳኑን ብቸኛ መሥዋዕት ኢየሱስ ክርስቶስን ቢክድ ወይም ቢተወው ስለኃጢአቱ የሚገባው ንስሐ ተቀባይነት የማያገኝና መዳንም እንደማይችል አስረድቶናል፡፡
- <u>*ማቴ 7:22-23::*</u> ‹‹በዚያ ቀን ብዙዎች፡፡ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል፡፡የዚያን ጊዜም፡፡ ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ፡፡››፣ <u>*ካል ቆሮ 13:5*</u> ‹‹5በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ፤ ወይስ ምናልባት የማትበቁ ባትሆኑ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ እንዳለ ስለ እናንተ አታውቁምን?›› በማለት የሚጠፉት ደግሞ እነማን እንደሆኑና በክርስትና ሃይማኖት ኑሮአችን ጥንቃቄ እንዲከበን ያስተምረናል፡፡

# <u>ኦርቶዶክሳዊት ቤ/ክ ስለ ፕሮቴስታንቲዝም ምን ትላለች?</u>

## *በ40ና በ80 ቀን (ሕጻናትን) ማጥመቅ*

- በቅዱስ መጽሐፋችን ከቤተሰቡ ወላጆች አንዳቸው በማመናቸው ድኅነት ለቤተሰቡ አባላት በሙሉ ይደረግላቸው እንደነበር ቃል የተገባላቸውን እናነባለን። ‹‹ኢየሱስም፦ እርሱ ደግሞ የአብርሃም ልጅ ነውና ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆኖለታል ›› *<u>ሉቃ 19:9።</u>*
- ከትያጥሮን ለመጣችው ቀይ ሐር ሻጭ ለነበረችው ለልድያም ‹‹እርስዋም ከቤተ ሰዎችዋ ጋር ከተጠመቀች በኋላ። በጌታ የማምን እንድሆን ከፈረዳችሁልኝ፥ ወደ ቤቴ ገብታችሁ ኑሩ ብላ ለመነችን፤ በግድም አለችን። ›› *<u>የሐዋ 16፡15።</u>*
- በዚሁ መሠረት የቤተሰቡ አካላት የሆኑት ሕጻናት እንዲሁ ቤተሰቦቻቸው አምነው የተቀበሉትን የክርስትና እምነት ተቀብለው በ40ና 80 ቀናቸው ይጠመቃሉ።
- ሕጻናትን የማጥመቅ የክርስትና ትምህርት በቀደሙት አባቶች ጽሑፍ በግልጽ ተገልጦ እናገኘዋለን።
- ሂፖሊተስ ‹‹አስቀድማችሁ ሕጻናቱን አጥምቁ ስለነርሱም ወላጆቻቸው ወይም ሌሎች ይናገሩላቸው።›› ሐዋርየዊ ትውፊት 21፡16 (216 ዓ.ም.)።
- ይህም በብሉይ እንደ ነበረውና ለጌታ የተቀደሰ በሚባሉበት፣ በ40ና በ80 ቀን ስጦታ ይዘው፣ ሕጻናቱን ታቅፈው  ወደ ቤተመቅደስ ይቀርቡ ከነበረበት የ ተገናኘም ነው።

# ኦርቶዶክሳዊት ቤ/ክ ስለ ፕሮቴስታንቲዝም ምን ትላለች?

## ቅዱስ ቁርባን

- ጌታችን የቅዱስ ቁርባንን ምስጢር በምሴተ ሐሙስ መስርቶልናል። *ማቴ 26፡26-28፣ ቀዳ ቆሮ 11፡23-25።*
- ‹‹*ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።*›› ዮሐ 6፡56።
- ቅዱስ ቁርባን በመቀበልም የአካሉ ብልቶች እንሆናለን። *ኤፌ 5፡30።*
- ቅዱስ ቁርባን በመቀበልም በመንፈስ፣ በቅድስናና በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነ ሕይወት እናድጋለን፣ ዘላለማዊ ሕይወትንም እንወርሳለን ‹‹*ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና።ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።ሕያው አብ እንደ ላከኝ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን፥ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል።ከሰማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነው፤ አባቶቻችሁ መና በልተው እንደ ሞቱ አይደለም፤ ይህን እንጀራ የሚበላ ለዘላለም ይኖራል*›› *ዮሐ 6፡54-58።*
- *ሥጋዊ ምግብን ስንበላ ሰውነታችን እንደሚጠነክርና ጤናማም እንደሚሆን መንፈሳዊውን ምግብ* የጌተችንን ቅዱስ *ሥጋውንና* ክቡር ደሙን ስንቀበልም ነፍሳችንን እናበረታለን የእግዚአብሔር የሆነው ጸጋም በውስጣችን *ያለማቋረጥ ያድጋል፣ ለሥጋችን፣* ለነፍሳችንና ለመንፈሳችንም መፍትሔን ይሰጣል። በቅዳሴ ‹‹›› ተብሎ እንደተገለጠው።

ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org